የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ.፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.41
ADDIS ABABA, 18th May, 2018

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፹፬/፪ሺ.፲ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ (ማሻሻያ) አዋጅ..............................ገፅ ፩ሺ.፫፻፷

**CONTENT**

Proclamation No.1084/2018

Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation…………………page 10360

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፹፬/፪ሺ.፲

## የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ.፯ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩.** **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፹፬/፪ሺ.፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No.1084/2018

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA PROCLAMATION

**WHEREAS**, it has become necessary to amend the Proclamation Defining the Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

   This Proclamation may be cited as the "Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation No.1084/2018".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪.ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ (እንደተሻሻለው) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ የአዋጁ አንቀፅ ፱ ንዑስ አንቀፅ (፯) እና (፰) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፯) ተተክቷል፤ ከአዋጁ አንቀፅ ፱ ንዑስ አንቀፅ (፱) እስከ ንዑስ አንቀፅ (፳፭) ያሉት ተከታታይ ንዑስ አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀፅ ፱ ንዑስ (፰) እስከ ንዑስ አንቀፅ (፳፬) ሆነው ተሸጋሽገዋል።

"፱(፯) የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር።"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፰ እና ፲፱ ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፰ ተተክተዋል፤ከአዋጁ አንቀፅ ፳ እስከ አንቀፅ ፵፩ ያሉት ተከታታይ አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀፅ ፲፱ እስከ አንቀፅ ፵ ሆነው ተሸጋሽገዋል።

"፲፰/ የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር።"

፩/ የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባሮች ፡-

ሀ) በአዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ (እንደተሻሻለ) ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እና ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች፣

ለ) በስራ ላይ ባሉ የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች እርሻን ፣የተፈጥሮ ሀብትን እና የእንስሳት ሃብትን በሚመለከት ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እና እንስሳትንና ዓሳ ሀብትን በሚመለከት ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር፣ ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች በዚህ አዋጅ ለግብርና እና እንስሳት

**2. Amendment**

The Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.916/2015 (as amended) is hereby amended as follows:

1/ sub Article (7) and (8) of Article 9 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub Article (7) of Article 9, and the subsequent Sub Articles 9 to 25 are renumbered as Sub Articles 8 to 24 of Article 9."

"9(7)The Ministry of Agriculture and Livestock Resources"

2/ Articles 18 and 19 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Article (18); and the subsequent Articles from Article 20 to Article 41 are renumbered as Articles 19 to 40.

"18/ The Ministry of Agriculture and Livestock Resources"

1) The powers and duties given to the Ministry of Agriculture and Livestock Resources :

a) The powers and duties given to the Ministry of Agriculture and Natural Resources and the Ministry of Livestock and Fisheries by Proclamation Number 916/2015 (as amended).

b) The powers and duties given to the Ministry of Agriculture and Natural Resources with respect to matters relating to Agriculture and Natural Resource and The Ministry of Livestock and Fisheries with respect to Livestock and Fishery by the provisions of other laws, currently in

ሀብት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

፫/ የአዋጁ አንቀፅ ፴፯ ንዑስ አንቀፅ (፯) እና (፰) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፯) ተተክተዋል፤ከአዋጁ አንቀፅ ፴፯ ንዑስ አንቀፅ (፱) እስከ ንዑስ አንቀፅ (፳፩) ያሉት ተከታታይ ንዑስ አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀፅ ፴፯ ንዑስ አንቀፅ (፰) እስከ ንዑስ አንቀፅ (፳) ሆነው ተሸጋሽገዋል።

"፴፯(፯) በአዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ (እንደተሻለ) እና በስራ ላይ ባሉ ሌሎች ህጎች ተጠሪነታቸው ለእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር እና ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር የነበሩ አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት በደንብ ይወሰናል።"

፬/ የአዋጁ አንቀፅ ፵ ንዑስ አንቀፅ (፬) እና ንዑስ አንቀፅ (፭) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፵ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተተክተዋል፤ከአዋጁ አንቀፅ ፵ ንዑስ አንቀፅ (፮) እስከ ንዑስ አንቀፅ (፲፫) ያሉት ተከታታይ ንዑስ አንቀፆች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀፅ (፭) እስከ ንዑስ አንቀፅ (፲፪) ሆነው ተሸጋሽገዋል።

"፵(፬) የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እንዲሁም የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች ለግብርና እና ለእንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ይሆናል።"

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵ ያፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

force, are hereby given to the Ministry of Agriculture and Livestock Resources.

3/ Sub Article (7) and (8) of Article 37 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub Article (7) of Article 37, and the subsequent Sub Articles 9 to 21 are renumbered as Sub-Articles 8 to 20 of Article 37."

"37(7) Executive organs which are accountable to the Ministry of Agriculture and Natural Resources and the Ministry of Livestock and Fisheries by proclamation number 916/2015 (as amended) shall be determined by a Regulation to be issued."

4/ Sub-Articles (4) and (5) of Article 40 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Article (4), and the subsequent sub-Articles 6 to 13 are renumbered as Sub Articles 5 to 12 of Article 40."

"40(4) The Rights and obligations of the Ministry Agriculture and Natural Resources and The Ministry of Livestock and Fisheries are hereby transferred to the Ministry of Agriculture and Livestock Resources: "

3. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 18th day of May, 2018**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**